# አንደበት ላጣ ሕዝብ!

(ከገሞራው)



ከነፃነት ሁሉ፣ ቀዳማዊቷ ዐይነት፣
የምላስ ነች አሉ፣ ናትና አንደበት፣
ተምኔቱን ምኞቱን፣ ሰው እሚገልጽባት!

ታፍኖ ከኖረ፣ የሰው ልጅ ምላሱ፣
እንኳን ስጋውና፣ ተገዥ ናት ነፍሱ!
የሚናገርበት፣ ብሶቱን ስቃዩን፣
አንደበት ከሌለው፣ ያ ሕዝብ የኛ ወገን፣
ቀላጤ ሊያሻው ነው፣ ተናጋሪ ልሳን!

ነፃ አገር ተሰዶ፣ ነፃነት ካለበት፣
ምንስ ማለት ይሆን፣ ትርጉሙ ነፃነት፣
አንደበት ላጣ ሕዝብ፣ ካልተናገሩለት!
ወንጀል አይሆንም ወይ፣ ወገኑ ነኝ ማለት?

መናገሪያው ልሳን፣ በግድ ታግቶበት፣
ዝምታ ቢውጠው፣ የዚያ ሕዝብ አንደበት፣
"ድርቅ ነው" እያሉ፣ ከሰጡ ምክንያት፣
ለራቡ ለሞቱ፣ ካሳበቡ በሳት፣
<u>ፈጅቶታል</u> ማለት ነው፣ እሪ በሉለት!!